# የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

# የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ማቋቋሚያና

# የአሰራር መመሪያ ቁጥር 91/2006

ግብር ከፋዩ ሕብረተሰብ በግብር አወሳሰን ላይ የሚኖረውን ቅሬታ የማቅረብ መብት በተገቢው ማስተናገድ እንዲቻል አስቀድሞ ይሰራበት የነበረው የአቤቱታ አቀራረብና አሰራር ሥርዓት የበለጠ ግልፅ ተደራሽና ፈጣን ማድረግ በማስፈለጉ፣

የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር በግብር/ታክስ አወሣሠን ላይ አቤቱታዎች ሲቀርቡለት በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ እንዲመረመር አድርጐ የመወሰን ሥልጣን የተሰጠውና ለዚህም ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴን አደረጃጀት፣ ተጠሪነት እና ከውክልና አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ተበታትነው ሲሰራባቸው የነበሩ የአፈፃፀም መመሪያዎች ማጠቃለል በማስፈለጉ፣

በዋና መ/ቤት በመመሪያ ተቋቁሞ የነበረውን ቴክኒክ ኮሚቴ ማፍረስ በማስፈለጉ፤

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በግብር/ ታክስ ሕጐች እና በማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 587/2000 በአንቀጽ 8(3) እና አንቀፅ 20(2) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይኸን የአፈፃፀም መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ማቋቋሚያና የአሰራር መመሪያ ቁጥር 91/2006 " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

2. **ትርጓሜ**

በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1/ "የግብር/ታክስ ህጎች" ማለት የባለስልጣን መ/ቤቱ ተፈጻሚ የሚያደርጋቸው የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 በአዋጅ ቁ. 608/2001 እና 693/2003 እንደተሻሻለ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 በአዋጅ ቁጥር 609/2001 እንደተሸሻለ፣የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 307/95 በአዋጅ ቁጥር 610/2001 እንደተሸሻለ፤ የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308/95 በአዋጅ ቁጥር 611/2001 እንደተሸሻለ፤የቴምብር ቀረጥ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 612/2001 ፤የማዕድን ስራዎች ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 53/1985 በአዋጅ ቁጥር 802/2005 እንደተሻሻለ፤የጫት ኤክሳይዝ አዋጅ ቁጥር 767/2004 የቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር 110/1990፤ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ደንብ ቁጥር 139/1999 ናቸው፡፡

2/ "ባለስልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ነው፡፡

3/ "ኮሚቴ" ማለት በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 104 ፣ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 40፣ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 307/1995 አንቀጽ 15 እና በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308/1995 አንቀጽ 18 እንድሁም በቴምብር ቀረጥ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 612/2001 አንቀጽ 2 መሰረት በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች እና እንደአስፈላጊነቱ በዋናው መስሪያ ቤት የሚቋቋም ኮሚቴ ሲሆን ከላይ በተገለጹት አዋጆችና ማሻሻያዎቻቸው መሰረት በባስልጣኑ በሚሰጡ የግብር/ታክስ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በመቀበልና በመመርመር ለባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይም ለሚወክለው የስራ ሀላፊ የውሳኔ ሀሳብ የሚያቀርብ ነው፡

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በግብር/ታክስ ህጎች መሰረት በሚሰጡ ውሳኔዎች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

4. <u>የኮሚቴው ተጠሪነት</u>

የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴው ተጠሪነት በዋና መ/ቤት ለባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይም ዋና ዳይሬክተሩ ለሚወክለው የስራ ኃላፊ በቅ/ጽ/ቤት ደግሞ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 19/1-2 መሠረት ይሆናል፡፡

5. <u>አደረጃጀት</u>

የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴው በዚህ መመሪያ በሚወሰነው መሰረት

1/ በባለስልጣኑ ዋና መ/ቤት እና/ወይም በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ይቋቋማል፡፡

2/ በዋና መ/ቤት ወይም በቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንደአስፈላጊነቱ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ሊቋቋም ይችላል፡

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ቢኖርም አንድ ጉዳይ በሁለት አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ሊታይ አይችልም፡፡

6. <u>የኮሚቴው አባላት</u>

1/ የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ከ3/ሦስት/ እስከ 5/አምስት/ አባላት ሲኖሩት

ሀ. ሰብሳቢ

ለ. አባል እና

ሐ. ጸሀፊ ይኖሩታል

7. <u>የኮሚቴ አባላትን ስለመሰየም</u>

1/ በዋና መ/ቤት የሚቋቋም ኮሚቴ አባላት በዋና ዳይሬክተሩ ወይም በሚወክለው የሥራኃላፊ ይሰየማሉ፣

2/ በቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሚቋቋም ኮሚቴ አባላት ኮሚቴው በሚቋቋምበት ቦታ የሚገኝ በዋና ዳይሬክተር በሚወከል የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ስራ አስኪያጅ አማካኝነት ይሰየማሉ፡፡

3/ የኮሚቴ አባል የስራ ዘመን ሁለት ዓመት ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ ለአንድ ተከታይ የስራ ዘመን ብቻ ሊያገለግል ይችላል፡፡

4/ የኮሚቴው ጸሀፊ የኮሚቴውን ስራ በመደበኛነት የሚያከናውን ሲሆን ሌሎች አባላት እንደአስፈላጊነቱ ከመደበኛ ስራቸው ጋር በመደረብ ወይም በመደበኛነት የኮሚቴውን ስራ እንዲሰሩ ይደርጋል፡፡

8. <u>የኮሚቴው አሰራር</u>

ኮሚቴው

1/ ከአባላቱ አብዛኛው ሲገኙ ምልአተ-ጉባኤ እንደተሟላ ይቆጠራል፡፡

2/ በተሟላ ምልአተ ጉባኤ በአብዛኛው የተደገፈው የውሳኔ ሀሳብ የኮሚቴው የውሳኔ ሀሳብ ሲሆን፣ድምጹ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ በሰብሳቢው የተደገፈው ሀሳብ የኮሚቴው የውሳኔ ሃሳብ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የኮሚቴው ስልጣንና ተግባር</u>

9. <u>የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴው ጠቅላላ ስልጣንና ተግባር</u>

ኮሚቴው ፡-

1/ በባለስልጣኑ ቅ/ጽ/ቤት የመጨረሻ የሆነ የግብር/ታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ለግብር ከፋዩ በተሰጠበት ጉዳይ የውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰ በ10 /አስር/ ቀናት ውስጥ በግብር/ታክስ ከፋዩ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን የመቀበልና የመመርመር፣

2/ የምስክር ወረቀት ለመከልከሉ ወይም የንግድ ስራ ፈቃድ ለመሰረዙ በተሰጡ ውሳኔዎች ቅር በመሰኘት የሚቀርቡ አቤቱታዎች ፤

3/ በግብር/ታክስ ከፋዮች መቀጫ እንዲነሳ፣ ወለድ ቀሪ እንዲደረግ ወይም የግብር ግዴታ እንዲሻሻል የሚቀረቡ ማመልከቻዎችን በመመርመር የውሳኔ ሃሳብ የማቅረብ፣

4/ ባለስልጣኑ የሰጠው የግብር/ታክስ ውሳኔ ትክክለኛ የተሟላ እና አዋጅን ደንብን መመሪያን ጠብቆ የተሰራ መሆኑን የማረጋገጥ፤

5/ ከቀረቡት አቤቱታዎች ጋር ግንኙነት ያላቸውን ማናቸውም የጹሁፍና የሰነድ ማስረጃዎች እንዲቀርቡለት የማድረግ፣ እንደአስፈላጊነቱም መስረጃው ወይም መረጃው በሚገኝበት ቦታ በመሄድ የመመልከት፣

6/ በማጣራት ሂደት ላይ የሚገኘውን ጉዳይ በሚመለከት ከግብሩ አወሳሰን ወይም ቀጥታ ባልሆነ መንገድ ግንኙነት ያለውን ሰው ለጥያቄ የመጥራት፣

7/ ከግብር /ታክሰ አወሳሰን ጋር በተያያዘ ለተመሳሳይና ተደጋጋሚ ቅሬታዎች መንስኤ የሆኑ ግድፈቶች የማስተካከያ ወይም የማሻሻያ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችሉ የመፍትሄ ሀሳቦች ማቅረብ ፡፡

10. <u>በዋና መ/ቤት የሚቋቋመው ኮሚቴ ሥልጣን</u>

በዋና መ/ቤት የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ መርምሮ የውሳኔ ሀሳብ የሚያቀርበው፡-

1/ ከፍተኛ ግብር ከፋይ የሆነና የተወሰነበትንና ለአቤቱታ መነሻ የሆነው/ወይም አከራካሪ የሆነው የታክስ መጠን ወለድና መቀጫን ጨምሮ ከብር 10,000,000.00/አስር ሚሊዮን/ በላይ ከሆነ ወይም

2/ መካከለኛ ግብረ ከፋይ የሆነና የተወሰነበትና ለአቤቱታ መነሻ የሆነው ወይም አከራካሪ የሆነው የገንዘብ መጠን ወለድና መቀጫን ጨምሮ ከብር 1,000,000.00/አንድ ሚሊዮን / በላይ ወይም፣

3/ አነስተኛ ግብር ከፋይ የሆነና የተወሰነበትና ለአቤቱታ መነሻ የሆነው ወይም አከራካሪ የሆነው የገንዘብ መጠን ወለድና መቀጫን ጨምሮ ከብር 100,000.00/አንድ መቶ ሺ/ በላይ የሆኑ ጉዳዮችን ብቻ ነው፡፡

## 11. <u>በቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሚቋቋም ኮሚቴ ሥልጣን</u>

በቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሚቋቋም ኮሚቴ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 10 መሰረት በዋና መስሪያ ቤት ከሚታዩት ጉዳዮች ውጭ የሚቀርቡትን አቤቱታዎች መርምሮ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

## 12. <u>የውሳኔ ሀሳብ ሰለማቅረብ</u>

1/ በዋና መ/ቤት የሚቋቋም ኮሚቴ ለዋና ዳይሬክተሩ ወይም ለሚወከለው የሥራ ኃላፊ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፣

2/ በየቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሚቋቋም ኮሚቴ በዋና ዳይሬክተሩ ለሚወከለው ሥራአስኪያጅ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባሉ፣

## 13. <u>የኮሚቴው የውሳኔ ሀሳብ ይዘት</u>

ኮሚቴው የሚያቀርበው የውሳኔ ሀሳብ፡-

1/ የቀረበው አቤቱታ በሚመረመርበት ወቅት የአቤቱታውን ይዘት፤የተያዙ ጭብጦች በሚመለከት፤ የተሰበሰቡ፣ የተገናዘቡ፣ የተመለከታቸው መረጃዎችንና ማስረጃዎች/ሰነዶች እንዲሁም አስቀርቦ በጠየቃቸው ሰዎች የተሰጡ አስተያየት ፍሬ ነገሮች ባጭሩ፣

2/ የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ በሚመለከት የሃሳብ ልዩነት ካለ ይሄንኑ ያካተተ እና፣

3/ የውሳኔ ሀሳቡን ባቀረቡት የኮሚቴ አባላት ፊርማ የተረጋገጠ መሆን አለበት፡፡

14. <u>የውሳኔ አሰጣጥ</u>

1/ ዋና ዳይሬክተሩ ከኮሚቴው የቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብ ማጽደቅ፤ማሻሻል፤የውሳኔ ሀሳቡን ካልተቀበለ እንደገና እንዲታይ መመለስ ይችላል፡፡

2/ በዋና መ/ቤት የሚቋቋም ኮሚቴ የሚያቀርበው የውሳኔ ሀሳብ በዋና ዳይሬክተሩ ወይም በሚወክለው የሥራ ኃላፊ ሲጸድቅ የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴው ውሳኔ ይሆናል፣

3/ በቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሚቋቋም ኮሚቴ ያቀርበው የውሳኔ ሀሳብ ዋና ዳይሬክተሩ በሚወክለው የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ ሲጸድቅ የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴው ውሳኔ ይሆናል፣

15. <u>የኮሚቴው ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት</u>

1/ የኮሚቴውን ጽ/ቤት ይመራል፣ ጽ/ቤቱም በቁሳቁስና በሰው ኃይል እንዲሟላ ያደርጋል፣

2/ ኮሚቴው በሚያደርገው የማጣራት ሂደት ከቀረቡት አቤቱታዎች ጋር ተያያዥነት ያላቸው መረጃዎች ከሚመለከታቸው አካላት እንዲቀርቡለት ይጠይቃል ያስጠይቃል፡፡

3/ በማጣራት ሂደት ላይ የሚገኘውን ጉዳይ በሚመለከት ወይም ከግብሩ አወሳሰን ጋር በቀጥታ ወይም ቀጥታ ባልሆነ መንገድ ግንኙነት ያለውን ማንኛውንም ሰው ኮሚቴው መጥራት እንዳለበት ሲያምን እንደአስፈላጊነቱ በጹሁፍ ወይም በቃል እንዲጠራ ያደርጋል፣

4/ ሰብሳቢው በማይኖርበት ወቅት ከአባላቱ አንዱን ሰብሳቢ እንዲሆን መወከል ይችላል፡፡

16/ <u>የኮሚቴው ጸሀፊ ተግባርና ኃላፊነት</u>

የኮሚቴው ጸሀፊ

1/ በለባስልጣኑ የግብር/ታክስ ውሳኔ ላይ ለኮሚቴው የሚቀርቡ አቤቱታዎች ለአቤቱታ ማቅረቢያ በተወሰነው የጊዜ ገደብ መቅረባቸውን በማረጋገጥ ይቀበላል፣

2/ ከኮሚቴው ሰብሳቢ ጋር በመመካር የስብሰባ አጀንዳ ያዘጋጃል፣

3/ ለኮሚቴው የቀረቡ አቤቱታዎች በአቤቱታ አቅራቢዎች ስም በተከፈቱ ማህደሮች መዝግቦ ይይዛል፣

4/ የየስብሰባውን ቃለ ጉባኤ ይይዛል፣ የኮሚቴውን የውሳኔ ሀሳብ ያዘጋጃል፣ አባላቱን በማስፈረም ለዋና ዳይሬክተር ወይም ለተወከለው ሰው ያቀርባል፤

5/ በዋና ዳይሬክተር/በተወካዩ የጸደቀ የውሳኔ ቅጂ ለአቤቱታ አቅራቢውና የግብር/ታክሱን ውሳኔ ላስተላለፈው የባለስልጣኑ የስራ ክፍል እንዲደርስ ያደርጋል፣

6/ ለኮሚቴው የሚቀረቡ አቤቱታዎችን እስታስቲካዊ መረጃ ይይዛል፣ሪፖርት ያጠናቅራል፣

7/ እንደአስፈላጊነቱ ከኮሚቴው ሰብሳቢ የሚሰጡ ሌሎች ስራዎችን ያከናውናል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የአቤቱታ መብትና አቀራረቡ</u>

17. <u>የግብር ውሳኔን በመቃወም አቤቱታ የማቅረብ መብት</u>

1/ ማንኛውም ግብር ከፋይ የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ የደረሰውና በግብር አወሳሰኑ ቅር የተሰኘ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ በተጠቀሰው ጊዜ አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው፡፡

2/ አቤቱታው ተቀባይነት የሚኖረው ግብር ከፋዩ የውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰው በ10 /አስር/ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ሲያቀርብ ነው፡፡

18. <u>የአቤቱታ ማመልከቻ ይዘት</u>

የአቤቱታ ማመልከቻው፤

1/ የግብር ከፋዩን ስም፣ አድራሻና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣

2/ ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ፍሬ ነገር እና የይግባኙን ምክንያቶች፣

3/ አከራካሪ የሆነውን የገንዘብ መጠንና የውሳኔ ማስታወቂያውን ያወጣውን ቅ/ጽ/ቤት ሊያካትት ይገባል፡፡

4/ የግብር ውሳኔ ማስታወቂያውን ትክክለኛ ግልባጭ እና ለአቤቱታው ማስረጃ ይሆነኛል የሚለውን አብሮ ያቀርባል፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ /1/-/4/ የተጠቀሱት ካልተሟሉ አቤቱታው ተመዝግቦ የቀረው ነገር ተሟልቶ እንዲቀርብ ሊመለስ ይችላል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

19. <u>ውክልና ስለመስጠት</u>

1/ በቅርንጫፍ ጽ/ቤት የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴን የማቋቋምና በኮሚቴው የሚቀርበውን የውሳኔ ሀሳብ የማጽደቅ ሥልጣን የየቅርንጫፍ ጽ/ቤት ስራ አስኪያጆች በዚህ መመሪያ ውክልና ተሰጥቷቸዋል፡፡

2/ የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ስራ አስኪያጆች በማይኖሩበት ጊዜ ምክትል ስራ አስኪያጅ እንደተወከለ ይቆጠራል፡፡

3/ በዋና መ/ቤት የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴን የማቋቋምና ኮሚቴው የሚያቀርበውን የውሳኔ ሀሳብ የማጽደቅ ስልጣን ውክልና በጽሁፍ ይሰጣል፡፡

## 20. ሪፖርት ስለማቅረብ

1/ የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ስላከናወናቸው ተግባራት፣ ስላጋጠሙት ችግሮችና የመፍትሄ ሀሳቦች አመታዊ ወይም እንደአስፈላጊነቱ ወቅታዊ ሪፖርት፤

ሀ. በዋና መ/ቤት የሚገኝ ኮሚቴ ለዋና ዳይሬክተሩ፣

ለ. በቅርንጫፍ የሚገኙ ኮሚቴ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያጸድቅ ለተወከለው ኃላፊ ሪፖርት ያቀርባል፣

2/ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያጸድቅ በዋና ዳይሬክተር የተወከለ ኃላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/1/ መሰረት ለዋና ዳይሬክተሩ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

## 21. የተሻረ መመሪያ

1/ ሐምሌ 14 ቀን 1998 ዓ.ም በፌደራል አገር ውሰጥ ገቢ ባለሥልጣን ወጥቶ ነበረው አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ የተሸሻለ የአሰራር መመሪያ ተሽሯል፡፡

2/ በህግ የተሰጠ የመወከል ስልጣንን ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 68/2004 እና መመሪያቁጥር 77/2004 እንድሁም በቁጥር1.0/388/13 ህዳር 20 ቀን 2005ዓም በተጻፈ ደብዳቤ ሸኘነት የተላከው መመሪያ ቁጥር 85/2005 ተሽረዋል፡፡

## 22. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1/ ቀደም ሲል በቅ/ጽ/ቤቶች አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ተጀምሮ የነበረ ማናቸውም አቤቱታ በነበረበት ሁኔታ በዛው ውሳኔ ያገኛል፡፡

2/ ይህ መመሪያ ጸድቆ ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት በነበረው መመሪያ መሰረት የቀረቡ አቤቱታዎችና ለቴክኒክ ኮሚቴ ቀርበው ውሳኔ ሳያገኙ በእንጥልጥል ያሉ ጉዳዮች በሙሉ በሚመለከተው አካል ታይቶ በልዩ ሁኔታ ውሳኔ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

23. ***መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ***

*ይህ መመሪያ በባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡*

አዲስ አበባ ህዳር 21 ቀን 2006 ዓ.ም

በከር ሻሌ
የኢትዮጲያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
ዋና ዳይሬክተር